 የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

# የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የህግ ማዕቀፎችመዋቅር እና አግባብነት

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ቁጥጥር የሚደረግበት የተማከለ የካፒታል ገበያ መመስረቱ በሀገሪቱ የፋይናንስ ዝግመተ ለውጥ ውስጥ ወሳኝ ጊዜን ያሳያል። ይህ ጽሁፍ የኢትዮጵያን ጅምር የካፒታል ገበያ የሚቆጣጠሩ የህግ ማዕቀፎችን በተለይም በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 እና ለአፈጻጸም የወጡ መመርያዎች ላይ አፅንዖት ይሰጣል። እነዚህ የህግ ማዕቀፎች ከኢትዮጵያ የልማት እቅዶች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በመገምገም የኢንቨስተሮችን ጥበቃ ከገበያ ተደራሽነት ጋር እንዴት ማመጣጠን እንደሚቻል፣ ተቋማዊ ተዓማኒነትን ከግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ጋር እና ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ከሀገር ውስጥ ነባራዊ እውነታዎች ጋር ይቃኛል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የህግ ማዕቀፍ ከዘርፉ አለም አቀፍ መርሆዎች ጋር ጠንካራ ቁርጠኝነት ያለው በመሆኑ የህግ ማዕቀፎቹን ወደ ተግባር ማሳደግ ለገበያ ስኬት አስፈላጊ የሆነውን እምነት፣ ተሳትፎ እና የገንዘብ ፍሰት በማሳደግ ችሎታቸው ላይ ይመሰረታል።

## ዘመናዊ የፋይናንሺያል ሥርዓት ሕጋዊ መሠረት

ለበርካታ አስርት ዓመታት የኢትዮጵያ የፋይናንስ ምኅዳር በውስንነት ይገለጻል። በመንግስት እና በግል የንግድ ባንኮች በበላይነት የተያዘው ባንክን ያማከለ ስርዓት ለካፒታል ማሰባሰብያ መንገድ ቀዳሚው እና ብቸኛው መንገድ ሆኖ ቆይቷል። የአጭር ጊዜ ብድር የበላይነት ይዞ በቆየበት የፋይናንስ ሥርዓት የረጅም ጊዜ የኢንቨስትመንት ካፒታል ማግኘት እጥረት ያለ ሆኖ ቀጥሏል። ከዚህ ቀደም የነበረው የአክሲዮን ገበያ የአክሲዮን ግብይት በንግድ ህጉ ጥንታዊ ድንጋጌዎች ሲመራ የቆየ እንደመሆኑ የኢንቨስተሮች ጥበቃ ዘዴዎች እና ግልጽ የዋጋ ግኝት ሥርዓት የሌለው ነው።

በአብዛኛው በባንክ አሰራር የተመሰረተው የኢንቨስትመነት ካፒታል አሰባሰብ ዘዴ መቀየር የጀመረው የኢትዮጵያ መንግስት የካፒታል ገበያ ልማትን በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ ቀርጾ ተግባራዊ ማደረግ ሲጀምር ነው። የካፒታል ገበያ ከአጭር ጊዜ የብድር ስርዓት ወደ የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት አማራጭ የሚያሸጋግር ባለቤትነትን፣ ፈጠራን እና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ሊፈጥር የሚያስችል ሥርዓት ነው። ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያዎች አንዱ የሆነውን የካፒታል ገበያ ተግባራዊ ለማድረግ የወጣው የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣንን የካፒታል ገበያ ስነ-ምህዳር ተቆጣጣሪ ተቋም እንዲሁም የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት በዚህ ዙሪያ የሚነሱ አለመግባባቶችን እንዲፈታ አቋቁሟቿል።

ይህ ጽሁፍ ከዚህ እናት ህግ የወጡትን ለአፈጻጸም የሚረዱ መመሪያዎች ይመረምራል። ዋና ዋና የህግ መሳሪያዎችን፣ የሚፈጥሩትን ተቋማዊ አርክቴክቸር እና ከሁሉም በላይ ከኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ለውጥ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይዳስሳል። ዋናው ጥያቄ ሕጎቹ መኖራቸው ብቻ ሳይሆን ለሀገራዊ ዓላማ የሚስማሙ መሆናቸውን፣ ለገበያ ተሳታፊዎች ተደራሽነታቸው፣ ከኢንቨስተር ጥበቃ፣ ከዓለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ እና ከኢትዮጵያ ልዩ የዕድገት አውድ ጋር አብረው የሚሄዱናቸው ወይ የሚለው ነው።

## የካፒታልገበያ አዋጅ

የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 የኢትዮጵያን የካፒታል ገበያ ስነ-ምህዳር የሚመራ ተቀዳሚ ህግ ሆኖ ያገለግላል።

በአዋጁ መግቢያ እንደተገለጸው ለአዋጁ መውጣት እንደምክንያት ከተጠቀሱት ውስጥ የገበያውን ፍትሃዊነት፣ ታዓማኒነት እና ቅልጥፍና ለማረጋገጥና ኢንቨስተሮችን ለመጠበቅ የካፒታል ገበያን ስነ-ምህዳር አዋጁ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣንን ራሱን የቻለ የፌደራል ተቆጣጣሪ አካል አድርጎ ያስቀመጠ ሲሆን ተጠሪነቱም በቀጥታ ለክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው። ይህ አዋጅ የካፒታል ገበያ ከገንዘብ ፖሊስ የቁጥጥር ሥርዓት የተለየ መሆኑን በመረዳት ለካፒታል ገበያ ቁጥጥር ሥርዓት እውቅና በመስጠት እና ከብሔራዊ ባንክ የቁጥጥር ሥርዓት አወቃቀር በመለየት ዘርፉ የተለየ እውቀት ባላቸው ባለሙያዎች እና የአሠራር ነፃነት ባለው ተቋም እንዲመራ ፈቅዷል።

# የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የህግ ማዕቀፎችመዋቅር እና አግባብነት

## የቁጥጥር ዋና ዓላማዎች

ባለሥልጣኑ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ውስጥ ያለውን ሚና የሚገልጹ ዋና ዋና ዓላማዎች በአዋጁ ተመልክተዋል። ከእነዚህ ውስጥ ዋነኛው ኢንቨስተሮችን መጠበቅ ሲሆን ይህም በገበያው ውስጥ ያሉ ተዋንያን በራስ መተማመን እና ደህንነት ተሰምቷቸው እንዲሳተፉ ማረጋገጥ ነው። ባለሥልጣኑ በአዋጁ ከተሰጠው የግል ኃላፊነትን ከመወጣት ባሻገር ጠንካራ የካፒታል ገበያ ሥነ-ምህዳርን ይገነባል። ይህም ሲባል ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች የሚወጡበት እና ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ እና ግልጽ በሆነ መንገድ የሚገበያዩበት ሥርዓት ይዘረጋል። ይህ ለታማኝነት የተሰጠው ቁርጠኝነት የዕለት ተዕለት ሥራዎችን ለመተግበር ብቻ ሳይሆን በካፒታል ገበያ ሊከሰቱነ የሚችሉ የስርዓት አደጋን በመቀነስም ጭምር የሚረዳ ነው። ይህም በገበያው ላይ ያለውን ታዓማኒነት የሚያጠናክር ነው።

በተጨማሪ የግብይት አሰራሮችን መዘርጋት እና የገበያ ታዓማኒነት ማስጠበቅ የፋይናንስ ስርዓቱን ከአለመረጋጋት ለመከላከል ይረዳል። የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንትን የሚስብ ምቹ የካፒታል ገበያ ሥነ-ምህዳር በመፍጠር ረገድ ባለሥልጣኑ፣ ዘላቂነት ያለውን የካፒታል ገበያን እድገት እንዲገነባ በአዋጁ ኃላፊነት ተጥሎበታል። እነዚህ የባለሥልጣኑ የቁጥጥር ዓላማዎች አንድ ላይ ሆነው ሚዛናዊ ተልእኮን የሚያንጸባርቁ ሲሆኑ ኢንቨስተሮችን ከለላ መስጠት፣ ፍትሃዊነትን እና ግልጽነትን ማረጋገጥ፣ተዓማኒነትን በመገንባት መዋቅራዊ የአደጋ ስጋቶችን መቀነስ እና የካፒታል ገበያን ማስፋፋት፣ የስርዓት መረጋጋትን መጠበቅ እና ዘላቂ ልማትን ማፋጠን የባለሥልጣኑ ብሎም በካፒታል ገበያ ውስጥ ያሉ ተቋማት አላማዎች ናቸው ብሎ መውሰድ ይቻላል።

## ከዓለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር መጣጣም

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ሕግ አውጭ አካሄድ ጉልህ ገጽታ ከዓለም አቀፍ ደረጃዎች እና መርሆዎች ጋር የተናበበ ነው። አዋጁ እና ለአፈጻጸም የወጡ መመሪያዎች በአለም አቀፍ ደረጃ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መርሆች እና ደረጃዎች አውጪ በሆነው የአለም አቀፍ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ተቆጣጣሪዎች ማህበር የወጡትን መርሆዎችን እና ደረጃዎችን በማጣቀሻነት የተዘጋጀ ነው። የአካዳሚክ ጥናቶች የሚያመለክቱት የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የህግ ማዕቀፍ ከአለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮ ጋር የተናበበ እና ሀገር ውስጥ ያለውን ነባራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ነው።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አዋጅ ሲቀረጽ አለም አቀፍ ደረጃዎችን፣ መርሆዎችን እና የተለያዩ ሀገራት ምርጥ ተሞክሮዎች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባቱ በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ደንቦችና አሠራሮች ውስጥ የተካተቱት የሕግ ማዕቀፎችና የማስፈጸሚያ ዘዴዎች የዳበረ ልምድ ካላቸው ያደጉ ሀገራት እና ዓለም አቀፍ ደረጃዎች ጋር ሲነፃፀሩ ምን ያህል ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ዝርዝር ጥናት በማድረግ የተካተቱ መሆኑን ልብ ይለዋል።

## ተቆጣጣሪዎቹ እና ተግባሮቻቸው

### የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ሥነ-ምህዳር ባለሥልጣኑ ሁሉን አቀፍ የቁጥጥር ስልጣን ተሰጥቶታል። ባለሥልጣኑ በአዋጁ የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር በተመለከተ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያን፣ የኢንቨስትመንት አማካሪዎችን፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላሎችን እና አከናዋኞችን፣ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አከናዋኞችን እና ሌሎች የገበያ ተዋናዮችን ፍቃድ መስጠትን፣ ለህዝብ ሽያጭ የቀረቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መመዝገብን፣ ማሳወቅን እና የአፈጻጸም መስፈርቶችን ማክበርን መቆጣጠር እና የህግ ጥሰትን በተመለከተ ቅጣት መጣልን ያጠቃልላል።

የባለሥልጣኑ የቁጥጥር ሥርዓት መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣንን የሚያካትት ሲሆን ይህም የአዋጁን ጥቅልል ድንጋጌዎች እና መስፈርቶች በዝርዝር ለመግለጽ ያስችላል። በባለሥልጣኑ የወጡ ቁልፍ መመሪያዎች የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁ.980／2016፣ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለሕዘብ ማቅረብ እና የግብይት መመሪያ ቁ.1030／2017፣ ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ

የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድቤት

# የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የህግ ማዕቀፎችመዋቅር እና አግባብነት

ድርጅቶች እውቅና አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ ቁ.1031／2017፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ፣ የተዛማጅ ውሎች እና ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ፈቃድ አሰጣጥ፣ አሰራር እና ቁጥጥር መመሪያ ቁ.1009／2017፣ለሕዝብ የሚቀርቡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ግዑዝ አልባ ማድረግ መመሪያ ቁ.1047／2017 እና በአሁኑ ወቅት በህዝብ ምክክር ላይ ያሉ የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ አስተዳደር ረቂቅ መመሪያ እና የካሳ ፈንድ የሚኒስትሮች ም／ቤት ረቂቅ ደንብ ይገኙበታል።

## የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ

የበባለሥልጣኑ ፍቃድ የተሰጠው ሥራ የጀመረው የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ በአዋጁ አንቀፅ 30 እና 31 መሰረት ራሱን የሚቆጣጠር ድርጅት (SRO) ሆኖ ይሰራል። በአዋጁ እንደተመለከተው ራሱን በራሱ የሚቆጣጠር ድርጅት ማለት የራሱን አባላቶች ፍትሃዊና ሀቀኛ እንዲሆኑ እንዲሁም በካፒታል ገበያው ቀልጣፋ አሰራር እንዲሰፍን እና የኢንቬስተሮች እና የህብረተሰቡ ጥቅም እንዲከበር ለማድረግ አባላቱ እንዲከተለ የሚገባቸውን የስነ-ምግባር ውስጠ-ደንቦች አውጥቶ በአባላቱ ቁጥጥር እንዲያደርግ በአዋጁ መሠረት እውቅና የተሰጠው ተቋም ነው። አዋጁ ለገበያው የአባልነት፣ የመመዝገቢያ፣ የግብይት እና የግጭት አፈታት ህጎችን በባለሥልጣኑ እያስጸደቀ እንዲያወጣ ስልጣን ይሰጣል። የገበያው የመተዳደሪያ ደንብ አምስት ጥራዞችን ያቀፈ ሆኖ አጠቃላይ ደንቦች፣ የአባልነት ደንብ፣ የምዝገባ ደንብ፣ የግብይት ደንብ እና የክርክር አፈታት ሂደቶች ያካተተ መሆኑን በባለፈው ጽሁፍ ተመልክተናል፡
የኢትዮጵያ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ በተለያዩ የግብይት ሰነዶች አይነት እና ደረጃ የተዋቀረ መሆኑ ለገበያ ልማት ሆን ተብሎ የተሰራ ንድፍ መሆኑን ያንፀባርቃል።

የአክሲዮን ገበያው በሁለት ደረጃ የተከፈለ ሲሆን ዋና የገበያ ቦርድ እና አዳጊ የገበያ ቦርድ ብለን ከነመስፍርቶቻቸው በባለፈው ጽሁፍ ያየናቸው ናቸው። ሌላው የቦንድ እና የአጭር ጊዜ የገንዘብ ገበያ ሰነዶች የሚገበያዩበት የግብይት ሥርዓት ሲሆን ሰነዶቹ በባህሪያቸው ቋሚ ገቢ የሚያስገኙ በመሆናቸው ገበያውም የቋሚ ገቢ ገበያ ተብሎ ይታወቃል። የኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ ሌላም አይነት አማራጭ የግብይት ሥርዓት ያቀረበ ሲሆን ይህም ከላይ የተጠቀሱ ቦርዶች ላይ መስፈርቶችን አሟልተው መመዝገብ እና መገበያየት ያልቻሉ ኩባንያዎች የሚገበያዩበት የራሱ ደንብ ያለው ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ እና ከህዝብ ገንዘብ የማሰባሰብ መድረኮችን የሚያካትቱ አማራጭ ገበያዎች ናቸው።በዚህ ረገድ ገበያው ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ዝርዝር የአሰራር ደንብ ያወጣ በመሆኑ በሌላ ጊዜ በሰፊው የምንመለስበት ይሆናል። የገበያውን መዋቅር በምናይበት ጊዜ የተለያየ ደረጃ ያለው ሆኖ መዋቀሩ አቅማቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ኮርፖሬሽኖችንም ሆነ ጀማሪ ትናንሽ ኢንተርፕራይዞችን ለማካተት እና ለማስተናገድ ያለመ መሆኑ አካታችነትን የሚያጎለብት እና ለትንንሽ ኩባንያዎች እንዲያድጉ እድል የሚያመቻች ነው ማለት ይቻላል።

## ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት

በብሔራዊ ባንክ ውስጥ የሚተዳደረው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ማከማቻ ግምጃ ቤት ለሰነደ ሙዓለ ንዋይ አያያዝ፣ ክፍያ እና ርክብክብ የቴክኖሎጂ አገልግሎት በመስጠት ክፍተኛ ሚና ይጫወታል። ግምጃ ቤቱ በኤሌክትሮኒክስ ሥርዓት የሰነዶች ባለቤትነት መዝገብ በመያዝ ከአክሲዮን የምስክር ወረቀቶች ጋር ተያይዘው የሚመጡ አደጋዎችን በማስቀረት የባለቤትነት መብትን በብቃት ማስተላለፍ ያስችላል። ይህም ድህንነቱ የተረጋገጠ ሰነደ ከመያዝ እና ከማስተላለፍ አንጻር ወሳኝ ሚና የሚጫወት ነው።

## የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

አዋጁ ከዓለም አቀፍ አሠራር ጋር በተጣጣመ መልኩ በነዚህ ተቋማት ውስጥ ኃላፊነቶችን ይደለድላል። ባለሥልጣኑ ግምጃ ቤቱን ጨምሮ ለገበያ ተዋናይ ፈቃድ በመስጠት የቁጥጥር ሥራ ያከናውናል፣ ገበያው በበኩሉ ኩባንያዎችን በመመዝገብ የግብይት ሥራውን በመስራት የራሱን ደንቦች ያስፈጽማል፣ ግምጃ ቤቱ ደግሞ መሰረተ ልማት በመጠቀም ከግብይት በኋላ የሚከተሉ የክፍያ እና የርክክብ ሥራዎችን ያከናውናል። ይህ የስልጣን ክፍፍል የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል እና በዘርፉ ያሉ ባለሙያዎችን እድገት ለማጎልበት የሚረዳነ ነው።

# የሰነድ ሙዓለ ንዋዮችቁጥጥር- ምዝገባ፣ይፋ ማድረግእና ቀጣይ ግዴታዎች

## የምዝገባ መስፈርት

የሕግ ማዕቀፉ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ ሽያጭ ከማውጣት አስቀድሞ በባለሥልጣኑ ሊመዘገብ እንደሚገባ የሚያዝ ሲሆን ይህም የአዋጁ የማዕዘን ድንጋይ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። የአዋጁ አንቀጽ 75(1) እና ሰነደ ሙዓለ ንዋይን ለሕዝብ ማውጣት እና ግብይት መመሪያ አንቀጽ 4 መሰረት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ለሕዝብ ሽያጭ ያወጡ፣ በማውጣት ሂደት ላይ ያሉ ወይም ለማውጣት የሚፈልጉ ኩባንያዎች ሰነዶቹን በቅድሚያ በባለሥልጣኑ እንዲመዘገቡ" ይደነግጋል።
ይህ የምዝገባ መስፈርት ዘርፉ ምንም ይሁን ምን ሁሉንም ኩባንያዎች የሚመለከት ነው። የምዝገባ ሂደቱ ዝርዝር የደንበኛ ሳቢ መግለጫ በመመሪያው አንቀጽ 77-134 ባሉት መስፈርቶች መሰረት በኢንቨስትመንት ባንክ ወይም አማካሪ እንዲዘጋጅ ማድረግ፣ ሌሎች ተጓዳኝ መረጃዎችን እና ሰነዶችን ማሟላት፣ በተፈቀደለት መኮንን ወይም የግብይት አማካሪ የተዘጋጀ የምዝገባ መግለጫ በማደራጀት ለባለሥልጣኑ የምዝገባ መጠየቂያ ሞልቶ ማስገባትን የሚያካትት ነው።

## የደንበኛ ሳቢ መግለጫ መስፈርቶች

የደንበኛ ሳቢ መግለጫበመረጃ ላይ የተመሰረቱ የኢንቨስትመንት ውሳኔዎችን ለማሳለፍ እንደ ዋና የመግለጫ ሰነድ ሆኖ ያገለግላል። በውስጡ የሚካተተው ይዘቱ የአውጪውን ሥራውን፣ የፋይናንስ አቋሙን፣ ለሽያጭ የቀረቡትን ሰነዶች እና ተያያዥ አደጋዎችን የሚመለከቱ ወሳኝ እውነታዎችን ያጠቃልላል። ዓላማው በቂ እና ትክክለኛ መረጃን በማቅረብ አቅም ያላቸው ኢንቨስተሮች በመረጃ ላይ የተመሰረተ የኢንቨስትመንት ውሳኔ እንዲያደርጉ ለማስቻል ነው። .
ይህ ይፋ ማድረግን ያማከለ የቁጥጥር እና የግብይት ሥርዓት አካሄድ ከሰነዱ አዋጪነት እና ጥራት ላይ ትኩርት ከሚሰጥ የቁጥጥር ሥርዓት ይልቅ በመረጃ ላይ መታመን ከዘመናዊው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ቁጥጥር ፍልስፍና ጋር ይጣጣማል።

ይህ አሰራር ባለሥልጣኑ አንድ ኢንቬስትመንት ጥሩ ወይም መጥፎ እንደሆነ ከሚወስን ይልቅ አዋጁ ሁሉም ወሳኝ መረጃዎች እንዲወጡ በማስገደድ የአዋጪነት እና የጥራት ጉዳይ የኢንቨስትመንት ውሳኔ በመሆኑ ለኢንቨስተሩ እንዲወሰን ይተዋል።

## ቀጣይነትያለው ሪፖርትየማድረግ ግዴታዎች

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ የአንድ ጊዜ ክስተት አይደለም። በአዋጁ አንቀጽ 77(1)(ሀ) እና በመመሪያው አንቀጽ 135(1) መሰረት ሰነዶቻቸው በሕዝብ የተያዙ ወይም ሰነዶቻቸውን ለሕዝብ ሽያጭ ያቀረቡ ኩባንያዎች ቀጣይነት ያለው ሪፖርት ለባለሥልጣኑ በየጊዜው እንዲያቀርቡ ይገደዳሉ።

እነዚህ ሪፖርቶች አንዳንዶቹ በየግማሽ ዓመት የሚቀርቡ ናቸው። አውጪዎች በሰነዳቸው ዋጋ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል ወሳኝ መረጃ በተከሰተ በ24 ሰዓታት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይጠበቅበታል። ይህ ቀጣይነት ያለው ወሳኝ መረጃዎችን ይፋ የማድረግ ስርዓት ኢንቨስተሮች ሰነዱን አውጥተው መሸጥ ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ ታሪካዊ መረጃዎችን ብቻ ሳይሆን የአሁናዊ መረጃ ማግኘት እንዲችሉ ይረዳል።

ለዚህ ጽሑፍ አላማ የያዝነው ትንታኔ ያላለቀ በመሆኑ በቀጣይ በዚሁ ርዕስ ከካፒታል ገበያ የሕግ ማዕቀፉ፣ መመሪያዎች አንኳር ነጥቦች በማንሳት በዝርዝር ማየት እንቀጥላለን፣ በመሆኑም በቀጣይ በጥልቀት የምንሄድበት መሆኑን በመግለጽ በዚሁ እንሰናበታለን።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT